# ኢትዮሚድያ

ልዩ ትንተና

(ትርጉም - ኦላና ኦብሴ)

# አንበሳውና ቀበሮው

------------------------------------------





መለስ ኦሞትን ወደ ካናዳ ሲልከው ሁለት መልክት አሲዞ ነው። ህሊናቸውን የሚሸጡትን በቀላሉ የሚታለሉትንና የሚደሉልትን ኦ'ኙዋኮች አግባብተህ ለእኔ አስገብር። እምቢ አንታለልም ያሉትን ደግሞ ከፋፍለህ እርስ በርሳቸው እንዳይስማሙ አድርግ።

ኦመት ወደ አሜሪካ ብቅ ሲል የውሸት መአት በከረጢት አጭቆ ንፁሃን ኦ'ኙዋኮችን ሲጨፈጭፍና ሲያስጨፈጭፍ በደም የጨቀየውን እጁን በነጭ እጅ-ከፈን (ግላቭ/ጉአንት) ሸፍኖ ነው። (ፎቶ - ከግራ ኦባንግና ጓደኞቹ፣ ከቀኝ ደግሞ ኦሉም ኦሙት ነው)

"ወደ ሀገራችሁ ወደ ጋምቤላ ኑ እና በገንዘባችሁ ስሩ። ኢትዮጵያ ዛሬ ብዙ ዕድል ያለባት ዲሞክራቲክ ሀገር ናት። ጋምቤላ ከመቸውም በላይ አድጋለች። ተሻሽላለች። ምንትሴ ቅብርጥሴ…".ሰሚ ያጣው ቅስቀሳው ባዶ ደካማና አሳዛኝ ነበር።

ኦሞት በታህሳስ 1995 ዓ.ም መንግስት በኦ'ኙዋኮች ላይ የፈፀመውን ጭፈጨፋና ጨፍጫፊዎቹም ለፍርድ ያለመቅረባቸው ጉዳይ ላይ ምንም ትንፍሽ አላለም። ለሱዳን ስለተሰጠውም መሬት ሆነ በሺህ ስለሚቆጠሩት ከእርስታቸውና ከትውልድ ቀያቸው በሱዳን የጦር ሀይል የሚፈናቀሉትን ኢትዮጵያውያንን አስመልክቶ ምንም የተናገረው ቃል የለም። ቀበሮውና አጀቦቹ ከካናዳ ድንበር ጭራቸውን ቆልፈው ወደ መጡበት ሰፈር እንዲመለሱ ተደርጓል። ካናዳ በጀግናው የኦ'ኙዋክ ተወላጅ ኢትዮጵያዊ ወጣት አንበሳ ኦባንግ ሜቶ ከቀበሮዎች ተርፋለች።

የኦ'ኙዋክ የፍትህ ምክር ቤትን መስርቶ ኦ'ኙዋኮች በቅጥረኛው በመለስ ዜናዊ መንግስት የሚድርስባቸውን ጭፍጨፋና መከራ ከአለም አለም እየዞረ ብሶታቸውን ያስተጋባው ኦባንግ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እየደረሰ ያለውን የሰብአዊ መብት ረገጣ ለማስቆም በሚደረገው ትግል ግንባር ቀደም መሪ በመሆን በአሜሪካ ምክር ቤትና በአወሮፓ ህብረት ወያኔ በዜጎቻችን ላይ እያደረሰ ያለውን ስቃይ ያጋለጠው ኦባንግ፣ በኢትዮጵያዊነቱና በኦ'ኙዋክ ተወላጅነቱ ዘወትር ኩራት የሚሰማው ፣ በጋምቤላ በእህቶቻችንና በወንድሞቻችን ላይ በደረሰው ጭፈጨፋ ላይ ዝም አላችሁ ብሎ ያሳፈረን ኦባንግ፣ የጋምቤላ ብሄረሰብ ከማናችንም በማያንስ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ለምንጠራጠር አላዋቂዎች የጋምቤላዎችን ፍፁም ኢትዮጵያዊነት ያስገነዘበን ፣ በኦ'ኙዋኮች ላይ የደረሰው ስቃይ መከራና ውርደት በሌሎችም ኢትዮጵያውያን ላይ እንዳይደርስ የሚታገለው ኦባንግ፣ በኦ'ኙዋኮች ላይ የተፈፀመውን ጭፍጨፋ በፊልም ቀርፆ "የዲሞክራሲ ክህደት" በሚል ስያሜ ወያኔ የፈፀመውን ጭፍጨፋ በማስረጃ ያቀረበው ኦባንግ ።

በኦባንግ ሜቶና በኦለም ኦመት የተደረገው ግብ ግብ በአንበሳውና በቀበሮው፣ በመልካምና በክፉ፣ በህብረት አንድነትና፣ በከፋፍለህ ግዛው መካከል ያሉ ልዩነቶችን የመተረክ ያህል ነው። በመጨረሻም መልካም በክፋት ላይ ድል እንደተቀዳጀ የሚያበስር ታሪክ ነው። ኦመት በዘር ላይ የተመሰረተውን ፌዴራሊዝምና እኩይ ዓላማ በውጪ ባሉ ወገኖች ላይም ተግባራዊ ለማድረግ በቅርቡ በጨለማው ንጉስ የተላከ የጥፋት መልክተኛ ነው። መለስ ዜናዊ ሰማንያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን ሰማንያ ሚሊዮን ቦታ በመከፋፈል

ለቁጥጥር እየተጠቀመበት ያለውን ዕቅድ ነው ይዞ የመጣው። መለስ በጭቆና ባህር የተከበቡ ጥቃቅን የጎሳ ደሴቶች የሞሉባትን ኢትዮጵያ እንደ ፈጠረ ሁሉ በውጪ ሀገር ባሉ ፤ ኢትዮጵያውያን መካከልም ይህንኑ ስልት በመጠቀም በተቃዋሚዎች ውስጥ ያለውን መከፋፈል ለመንግስት ቁጥጥር እንዲያመች የበለጠ ለማስፋት ነው።

እንደ አመት አይነት ቀበሮዎች "የጎሳ መሪዎች" በውጪ በሚገኙ ተቃዋሚዎች መካከል የሚነፍሰውን የፖለቲካ አየር እንዲያነፈንፉና እያንዳንዱን ቡድን/ክፍል ከመለስ ጋር ለማስማማት የሚያስችል ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ተላኩ። አኙዋኮችን በተናጠል ከመለስ ጋር ለማስታረቅ ኦመት ወደ አሜሪካ መጣ "የአማራ" ክልል ልዑካንም በያዝነው ወር መጨረሻ ላይ ተመሳሳይ መልዕክት ይዞ ወደ አትላንታ እየተንጋፈፈ ነው። መለስ በውጪ ያሉ ተቃዋሚዎች ተከፋፍለዋል፣ ተዳክመዋል፣ ወኔያቸው ሞቶ ተስፋ ቆርጠዋል የሚል ግምት ስላለው እነዚህን የጎሳ መሪዎች እንደ አሮጌ ጎማ ወዲያና ወዲህ ሲያሽከረክራቸው እንደሚከርም የታወቀ ነገር ነው። በርግጥም ተቃዋሚዎች በአንድ ላይ ባልቆሙበት ወቅት ለመለስ ከእያንዳንዱ ጎሳ ጋር በተናጠል ለመደራደር ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለኝም ይላል። ይህ ግን ባዶ ምኞት ነው። መለስ በሁሉም ላይ ጦርነት አውጆ በተናጠል ከእያንዳንዱ ጋር ዕርቅ ማድረግ አይችልም።

ከአንበሳውና ከቀበሮው ታሪክ ምን እንማራልን?
ትምሕርት አንድ

በመጀመርያ የተማርነው ታላቁ ትምሕርት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በዚች ሀገር ያለ ብሔረሰብ ብቻውን በራሱ የቆመ ደሴት ሳይሆን ሁሉም የባሕር ዘራፊዎች በሚቆጣጠሩት በአንድ መርከብ ላይ በጭቆና ባሕር ውስጥ የሚዋኘርቅ ሕዝብ ነው። አኙዋኮች ከኦሮሞዎች፣ ከአማራዎች፣ ከትግራይ ወይም አኙዋኮች ከሌላው ኢትዮጵያዊ ሕብረተሰብ ተለይተው ለብቻቸው ዕርቅ አያደርጉም። ችግራቸው ማን የማን ብሔረሰብ አባል ነው ሳይሆን፡ ችግራቸው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገን እየደረሰበት ያለው ችግር.. ፍትህ፣ ነፃነት፣ ዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት እጦት ነው። የአኙዋክን ሰላማዊ ሕዝብ የጨፈጨፉ አረመኔዎችን ለፍርድ አለማቅረብ ማለት አኙዋኮችን ብቻ ሳይሆን መላውን ኢትዮጵያዊ ፍትህ መከልከል ማለት ነው። የ193 ሰላማዊ ሰልፈኞች ገዳዮች ለፍረድ ሳይቀርቡ እንደልባቸው በየአውራጎዳናው ሲረመሰመሱና ሲፏነጩ ፍርድ የተነፈገው እገሌ ከገሌ ሳይባል ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በአፋር ክልል፣ በቤኒሻንጉል ግሙዝና በኦሮሞዎች ላይ የሚደርሰውን ስቃይ አኙዋኮችም ይጋሩታል። ችግሩ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ፍትህ ማጣት ነው። በደል የአኙዋክ፣ የትግሬ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ መልክ የለውም። የበደል መልኩ አንድ ብቻ ነው እርሱም ክፋት ነው።ከዚህ ከግብረገብነት ከተሞላው ታሪክ የተማርነው ክፋትና ጥቃት ሲዘነዘርብን እርስ በእርሳችን ከመጎነታተል በአንድነት ተባብረን ክፋትን መዋጋት አለብን።

ትምሕርት ሁለት

ከታሪኩ የምንማረው ሁለተኛው ጥሩ ምግባር ጨቋኞች አምሮአችንን ወደ ኋላ ጠምዝዘን ቀደምት ባለፈ ታሪክ የተፈጠረ ቅሬታ ላይ ደንዝዘን እንድንቀርና የወደፊት ብሩህ ተስፋችንን እንዳናይ ፍላጎታቸው ነው። ትናንትም ዛሬም አኙዋክ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ተጨቁነዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተበድለዋል፣ አድሎ ተደርጎባቸዋል። በ1995 አኙዋኮች በመለስ ሲጨፈጨፉ ጥቂቶቻችን ስልፍ ወጣን። ልናፍር ይገባናል! ለዚህ ተገቢ ምክንያትም አለ። አንድ አንድ አኙዋኮች ለረጂም ጊዜ በደረሰባቸው በደልና ብሔረሰባቸው ተረስቶና ተገልሎ በመቆየቱ ያማርራሉ። ቢያማርሩ አይፈረድባቸውም። አንዳንዶቹም የደረሰባቸው በደልና ስቃይ ጥልቅና መራር ከመሆኑ የተነሳ ኢትዮጵያዊነታቸውን አይፈልጉም። እጅግ በጣም እናዝናለን። ነገር ግን ላዘኑት ሁሉ የምንለው ቢኖር ከዚህ የተሻለ መንገድ እንዳለ ነው። የወደፊት መንገዳችንም ይሆናል። ይኸውም አብረን የምንገነባው በዲሞክራሲ በነፃነትና በሰው ልጆች መብት ላይ የተመሰረተ ጠንካራ ግንባታ ነው። ወንድ ሴት ሳይል፣ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖት ሳይለይ፣ ሀብታም ድሃ ሳይል፣ የእያንዳንዱን ግለሰብ መብት የሚጠብቅና ዋሰትና መስጠት የሚችል፣ ሁሉም በነፃነትና በደስታ

የሚኖርበት፣ መንግስት ህዝቡን እያስፈራራ የሚገዛበትን ሳይሆን መንግስት ሲያጠፉ የሚጠየቅበትን ሕዝቡን የሚፈራብትንና የሚያከብርበትን በአግባቡ የሚያገለግልበትን ስርዐት ለመፍጠር ነው።

ትምሕርት ሶስት

ሶስተኛው ትምሕርት የሰው ልጆችን መብት በማክበር ሌሎችም እንዲያከብሩ ተፅዕኖ በማድረግ ካናዳ የተጫወተችው ሚና ነው። ካናዳ ኦመትና ጋሻጃግሬዎቹን አላስገባም በማለት በገዳዮችና በደብዳቢዎች ላይ ቆራጥ እርምጃ ወሰደችባቸው። አንድ ለሰብአዊ መብትና ለዲሞክራሲ የቆመ ለሕግ እራሱን ያስገዛ መንግስት ማድረግ ያለበትን ካናዳ በማድረጓ ለሌሎች ዲሞክራት ነን ባዮችም እንደ ምሳሌ ሆናለች። ካናዳ ኦመትን ቪዛ የከለከለችው ኢትዮጵያ ውስጥ በደረሰው የሰው ዘር ማጥፋት ወንጀልና በጅምላ የሰው ልጆች መብት ጥሰቶች ውስጥ ቀጠተኛ ተሳታፊ ለመሆኑ በርካታ መረጃዎች ስላሉ ነው። ካናዳውያን ዛሬ ከኢትዮጵያውያን ጋር ጎን ለጎን መቆም ይችላሉ። ምክንያቱም ካናድያን የእኛ ውርደት ስቃይና መሰረታዊ መብት ማጣት እንደኛው ስለሚሰማቸው።
ከካናዳው ልምድ ከዚህም የላቀ ትምሕርት ይገኝበታል። በማንኛውም ሀገር ያለ ኢትዮጵያዊ ኦባንግ በካናዳ ውሰጥ ያደረገውን በሚኖርበት ሀገር ማድረግ ይችላል። በሰው ልጆች መብት ጥሰት የሚጠረጠሩ ካናዳ እንዳይገቡ ከታገዱና በኃይለኛዋ ብዕር ከተሸነቆጡ በእንግሊዝም፣ በፈረንሳይም፣ በጀርመንም፣ በጣልያንም፣ በስፔይንም፣ በግሪክም፣ በኔዘርላንድም፣ በአውስታርሊያም …ተመሳሳዩን ማድረግ ይቻላል።
ታዲያ ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ምን ትጠብቃላችሁ? ፈጥናችሁ ለስራ ትጉ!

ትምሕርት አራት

ከዚሁ ታሪክ የምንማረው አራተኛው ትምሕርት ዋነኛ ዓላማችንና የድካማችን ፍሬ የሆነው የሰብአዊ መብት HR 2003 የተሰኘው ረቂቅ ሕግ በአንቀስ 5 (A) (2) የተዘረዘረው በስራ ላይ መዋሉ ነው። እኛ በሕግ ልናደርግ የሞከርነውን ካናዳውያን በስልጣናቸው በቀላሉ አድረገውታል። ለኢትዮጵያ ባለስልጣኖች፣ የፀጥታ ሰራተኞች፣ ሰላማዊ ሰልፈኞችን የጨፈጨፉትን፣ በቃሊቲ እስር ቤት ያጎሩትን ወይም የሰው ልጆችን መብት በጅምላ በመጣስ የሚጠረጠሩትን ቪዛ መከልከልና አሜሪካ እንዳይገቡ ማገድ። ኦባንግ ይህንን የሰብአዊ መብት ረቂቀ ህግ HR 2003 ዋና አካል የሆነውን ደንብ በስራ ላይ በማዋሉ በሰሜን አሜሪካ ለምንገኝ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሰው ልጆችን መብት ረጋጮቹ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት እኛ በምንኖርበት ዲሞክራቲክ ሃገሮች ድርሽ እንዳይሉ ማሳገድ እንደምንችል ትልቅ ትምሕርት ስላስተማረን በጣም እናመሰግነዋለን።

ትምሕርት አምሰት

አምስተኛው ትምህርት የትብብርን ሀይል ብርታት ያስተምረናል። ሰዎች እንደ አንድ ሰው ለአንድ ተግባር ሆ ብለው ሲነሱ ውጤቱ በጣም አስደናቂ ነው። የድሕረገፅ አዘጋጆች፣ የሬዲዮ አስተናጋጆች፣ አስተያየት ሰጪዎችና የዋና ዋና የዜና አውታሮች ተወካዮች የበግ ለምድ ለብሰው የሚንቀሳቀሱ ቀበሮዎችን ለማጋለጥ ተረባርበዋል። ኦባንግ ሜቶ ብቻውን ያደረገው ነገር አይደለም። በካናዳና በአሜሪካ ካሉ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በካናዳ ካሉ የሰው ልጅ መብት ተከራካሪዎች፣ ከፓርላማ አባላቶች፣ ከጠበቆች፣ ከሀይማኖት መሪዎች፣ ከኮሚኒቲ መሪዎች፣ ከምሁራኖችና ከተራው ዜጋ ጭምር ትብብር ተደርጎለታል። ሁሉም ላደረጉልን ትብብር ምስጋናችን ይድረሳቸው።

ትምሕርት ስድስት

በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ ሀቅ እንማራለን። ኦመት እስከራሱ አምስት ሕፃናቸውን የሸጡ ካድሬዎችና አንድ ሀገር ወዳድ አርበኛ ይዞ ነው ወደ አሜሪካ የመጣው። አራቱን ይዞ ሲመለስ አርበኛው እዚሁ አሜሪካ ቀርቷል። ስሙም ኦባንግ ኦማን ይባላል። ለሰው ልጅ መብት በመቆሙ በጋምቤላ ውስጥ ብዙ ስቃይ የደረሰበት ወጣት ነው። ኦመት ተልዕኮው በሁሉም የተደገፈ ለማስመሰል ነው በዚህ በአሳፋሪ ተልኮው

የጨመረው። ሆኖም ግን ኦባንግ ኦማን ለሀቅና ለሀገሩ ያለው ታማኝነት ሀገር ቤት ተመልሶ ለሕዝቡ ዋሽቶና ቀላምዶ ከሚያገኘው ሀብት ስለበለጠበት ነው እዚህ የቀረው።

ኦባንግ ሜቶ
እና
ኦባንግ ኦማን
የክብር ሰላምታ እንሰጣችኋለን።

## ትምሕርት ሰባት

ቀበሮው በተፈጥሮው ጥንብ እየበላ የሚኖር ጥንብ አንሳ ነው። አንበሳ ደግሞ ኩራትና የክብር ምልክት ነው። ኦባንግንና የአኙዋክ የፍትህ ምክር ቤትን (ኤጄሲ) ልናመሰግን ይገባል። ከዚያም በላይ ልናግዝ ይገባናል። ኦባንግ ዕለት በዕለት በኢትዮጵያውያን ላይ የሚደርሰው ግፍና በደል ቆርቁሮት ኑሮውንና ትዳሩን ሰውቶ ለፍትህና ለሰው ልጅ መብት የሚታገል ሰው ነው። ለብዙ ዓመታት አብረነው ስርተናል። ኦባንግና ኤጄሲ ባይኖሩ ኖሮ ዛሬ ገሀድ የወጣውን በአኙዋክ ወንድሞችና እህቶቻችን ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋና ዛሬም እየደረሰባቸው ያለውን መከራ ማወቅ አንችልም ነበር። ኦባንግ ደጋግሞ የምክር ቤቱን በር ባያንኳኳ፣ ያለመታከትም የምክር ቤት ተመራጮችን በተደጋጋሚ ባይጎበኝና ጉዳዩን ከሰብአዊ መብት ተሟጋቾች፣ ታዛቢዎችና የመሳሰሉት ጋር ባያቀነባብረው ኖሮ የሰብአዊ መብት HR 2003 ዛሬ የደረሰበት ደረጃ አይደርስም ነበር። ኦባንግና AJC ኢትዮጵያ ውስጥ ለሰብአዊ መብት መከበር ያደረጉትን ታላቅ አስተወፅኦ አንድ ቀን ታሪክ ይዘግበዋል። ሆኖም ግን አንዳንዴ ወጣት አንበሶችም ከጓደኞቻቸው ዕርዳታ ይፈልጋሉ። ኦባንግና AJC ያበረከቱልንን አስተወፅኦ ከወደድን …… ገንዘባችን ትልቅ ቁም ነገር ላይ እንዲውል ከፈለግን ….መርዳት አለብን። የAJCን ዌብ ሳይት: http://www.anuakjustice.org/ በመጎብኘት መዋጮ እናድረግ።

ኦሞት ከዚህ ጥፋ! ገዳዮች ገራፊዎችና የሰው ልጅ መብት ገፋፊዎች ተጠንቀቁ! ዛሬ ካናዳ በሯን ዘጋችባችሁ። ነገ ደግሞ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ጣልያን፣ ስፔይን፣ ግሪክ፣ ኔዘርላንድ፣ ስዊድን፣ አውስትራሊያ…….. እና ……… ፊታችሁ ላይ በራቸውን ይጠረቅሙባችኋል። በየሄዳችሁበት ሁሉ ብዙ ኢትዮጵያውያን ኦባንጎች በዚህ ዜማ ያስተናግዱችኋል።

*"ቀበሮ ጥፋ ከዚህ እንዳትደርስ*
*በመጣህበት እግርህ ተመለስ።*
*የሽምጥ ጋልብ ቆልፈህ ጭራ -*
*ድርሽ እንዳትል ወደ እኛ ጎራ !"*